ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ

Wisdom at the Source of the Blue Nile

# በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር የ2006 ዓ.ም. የስራ እንቅስቃሴ አጭር መግለጫ

ሚያዝያ 2006 ዓ.ም




የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕ/ጽ/ቤት አካል የሆነው የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ክንፍ በዩኒቨርሲቲው የተከናወኑ ችግር ፈቺ ምርምሮችን ወደተለመላቸው ተጠቃሚዎች ለማድረስና የተፈለገውን የመጨረሻ ግብ ለመምታት የሚያስችሉ ቀልጣፋ የቴክኖሎጂ ማሸጋገሪያ ስልቶችን ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣምና በማበልጸግ የምርምር ውጤቶች ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያመጡ ለማስቻል በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የቴክኖሎጂ ሽግግር የትኩረት አቅጣጫዎች ባብዛኛው ቴክኖሎጂዎችን ከሚያፈልቁ የዩኒቨርሲቲው ምርምር ማዕከላትና አካዳሚክ ክፍሎች የምርምር ትኩረት አቅጣጫዎች ጋር የሚጣጣሙ ቢሆንም በፍጥነት ሊሸጋገሩ የሚችሉ፣ በገበያው ከፍተኛ ተፈላጊ የሆኑና ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን እውቀትን ሲያሸጋግር ከቆየባቸው መንገዶች በዋናነት የሚጠቀሱት የሰለጠነን የሰው ኃይል ለኢኮኖሚው ማበርከት፣ የምርምር ውጤቶችን ማሳተም፣ በምርምር ኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች መሳተፍና በመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ ተጠናክረውና አበረታች በሆነ መልኩ ቀጥለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ያለቀላቸውን ቴክኖሎጂዎች ለተጠቃሚው በፍጥነት ከማድረስ አኳያና በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተፈጠረን ዕውቀት ወይም በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችና ምርምር ተቋማት የተፈጠሩና ስራ ላይ የዋሉ ስራዎችን የተስማሚነት ወይም የማላመድ ጥናት በማካሄድ የሃገራችንን፣ የዩኒቨርሲቲውን፣ የማህበረሰቡን እንዲሁም የተመራማሪውን ገቢ ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ስልቶችንና መንገዶችን ለመጠቀም ተዘጋጅተዋል፡፡ ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማሳለጫ መንገዶች መካከል የሚከተሉት በውጤታማነታቸው በተለያዩ ባደጉና በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች ከተመሰከረላቸው መካከል ይገኛሉ፡፡

- የቴክኖሎጂ ቢዝነስ ኢንኩቤተሮች
- የፈጠራና የምርምር ቴክኖሎጂ ፓተንቶች ሽያጭ
- የጋራ ምርምርና የኮንትራት ማማከር ስራዎች
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፓርኮች

ዩኒቨርሲቲያችን እነዚህን የቴክኖሎጂ ሽግግር ማሳለጫ መንገዶች ጥቅም ላይ ለማዋል የውስጥ አሰራሮችን ለማሻሻልና መሰረተልማቶችን ለማቋቋም በቁርጠኝነት እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ሊሸጋገሩ የሚችሉና ያለቀላቸው ቴክኖሎጂዎችን ለሽግግር የማዘጋጀት ስራዎች ከወዲሁ እያከናወነ ይገኛል፡፡

በ2006 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ለማህበረሰቡ ይሸጋገራሉ ተብለው የሚጠበቁትና በሙከራ ደረጃ ላይ ያሉት ቴክኖሎጂዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በእጅ የሚሰራ (Manual) የካልሲ መስሪያ (sock knitting) ማሽን የዩኒቨርሲቲው ምርምር ስራ ውጤት ሲሆን ምርምሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ለሽግግር በሚሆን መልኩ ማሻሻያ እየተደረገለት ይገኛል፡፡ ስራው ሲጠናቀቅ መሳሪያው በ20 ደቂቃ ውስጥ አንድ ካልሲ ማጠናቀቅ እንደሚያስችል ተመራማሪው ገልጸዋል፡፡

2. የሃንድሉም ማሻሻያ ስራ በዩኒቨርሲቲው መምህር ተጠንቶ አበረታች ውጤት በማስገኘቱ የማሻሻያ ስራ እንዲያገኝ ድጋፍ ተደርጎለት እየተጠናቀቀ የሚገኝ ሲሆን በዓመቱ ተጠናቀው ለሽግግር ከሚዘጋጁት መካከል አንዱ ነው፡፡

3. የቲማቲም ድልህ ማቀነባበሪያ ማሽን በሌሎች ሃገራት በስራ ላይ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የቲማቲሙን ይዘት በማይጎዳና ፈጣን በሆነ መልኩ የቲምቲም ድልህ ለመስራት የሚያስችል፣ ማሽኑን በመስራት እንዲሁም የቲማቲምን እሴት ጨምሮ ለገበያ በማቅረብ መስማራት ለሚፈልጉ ዜጎች የገቢ ምንጭ ሲሆን የሚችል በመሆኑ ሊሸጋገሩ ከሚችሉ ቴክኖሎጂዎች መካከል አንዱ ሊሆን ችሏል፡፡

4. table top የምግብ ዘይት መጭመቂያ ማሽን

ማሽኑን አስመስሎ በመፈብረክና አፈጻጸሙን በመሞከር ስራ ላይ የተሰማሩ መምህራን ተስፋ ሰጪ ውጤት በማስመዝገባቸው የማሻሻያ በጀት ድጋፍ ስለተደረገላቸው በዚህ የትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ አጠናቀው ለማቅረብ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ ስራ ሲጠናቀቅ ከፍተኛ ዋጋና ጤናማ ንጥረነገር ያላቸው የቅባት እህሎችን በመጠቀም በዓለም የታወቁና ለጤና ተስማሚ የሆኑ ድንግል የምግብ ዘይቶችን (virgin edible oils) ማምረት ከማስቻላቸውም በተጨማሪ ሌሎች እንደ ጥቁር አዝሙድ፣ ድንብላልና የመሳሰሉ የቅመማ ቅመም ዘይቶችን ማምረት ያስችላል፡፡

5. የተሽከርካሪ ስምሪት መቆጣጠሪያና አሰራር ማሻሻያ ፕሮጀክት (GPS-GPRS based real time vehicle tracking and management system) በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪዎች ላይ ለሙከራ ሊሰራ የታቀደ ፕሮጀክት ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ ላይ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል፡፡ ይህ ስራ በሌሎች ተሽከርካሪ በሚያስማሩ መስሪያቤቶችና ባለሃብቶች የተሽከርካሪ ስምሪት አሰራር ለማሻሻል ተፈላጊነቱ ከፍተኛ በመሆኑ በፍጥነት ይሸጋገራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

6. በተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) መሰረታዊ የኮምፒዩተር እውቀትን ያለ አስተማሪና በአማርኛ ቋንቋ መማር የሚያስችል VCD በዩኒቨርሲቲው መምህራን ተዘጋጅቶ በመጠናቀቅ ላይ ያለ ሲሆን ለተጠቃሚው ለመሸጋገር በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

7. በፀኃይ ኃይል የታገዘ የdrip irrigation ሲስተም ዲዛይን ለማድረግና ለመተግበር እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው የ ዩኒቨርሲቲው ምርምር ቡድን በዚህ አመት መጨረሻ ስራውን ለማጠናቀቅና ለተጠቃሚዎች ለማስተዋወቅ እየሰራ ይገኛል፡፡

8. የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ አቀፍ ሬድዮ (FM 93.3) በዩኒቨርሲቲው መምህራን ዲዛይን ተደርጎ ያለቀ ሲሆን ከ ኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኤጀንሲ ፍቃድ በማግኘቱ የኢንተርኔት ስርጭቱን ጀምሯል የሬድዮ ስርጭቱንም ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነው፡፡ ይህ ስራ ሲጠናቀቅ የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ ኮምፒዩተር ሳያስፈልገው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየተሰራ ስላለው ስራ ማወቅና አስተያየቱን መስጠት የሚችልበት ሁኔታን ስለሚፈጥር ግዝባቤው እንዲዳብር ይረዳል፡፡

የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ሁል ጊዜ ገቢ ከማግኘትና የምርምር ውጤቶችን ከመሸጥ ጋር ብቻ የሚያያዙ ሳይሆኑ የቴክኖሎጂዎች መኖርን፣ ጠቀሜታቸውን ካለማወቅ እና ከአጠቃላይ ግንዛቤ እጥረት የተነሳ ኑሯቸውን ለማሻሻል ያልቻሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የአመለካከትና የግንዛቤ ለውጥ ለማምጣት ሲባል በቀላሉ ሊሰርጹ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ ስራ ሰርቶ በማሳየት ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣትና የመጣውንም ለውጥ ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት በመውሰድና በማስፋት ሃገራዊ ለውጥ ለማምጣት እንዲችሉ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሞዴልነት ይዞ የማህበረሰብ አገልግሎት እያበረከተ በሚገኝበት የቆለላ ሶላር መንደር ውስጥ የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ከሌሎች የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ጎን ለጎን እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

በ2006 ዓ.ም. በዚህ መንደር የተጀመሩት የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችም የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የፀኃይ ኃይልን በመጠቀም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን በጥላ የማድረቅ ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅ ስራ ተጀምሯል፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ አካባቢው የመስኖ ተጠቃሚ እንደመሆኑ መጠን በስፋት የሚመረቱትንና በከፍተኛ የርጥበት መጠናቸው የተነሳ በቶሎ የሚበላሹ እንደ ድንች፣ ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ በርበሬና የመሳሰሉ ምርቶች የንጥረ-ምግብ ይዘታቸው፣ ቀለማቸውና ወደነበሩበት የርጥበት መጠን የሚመለሱበት (reconstitutability) ሁኔታ ሳይጎዳ ለማድረቅ የሚያስችል ሲሆን በብዙ ሃገሮች ተሞክሮ ውጤታማ የሆነ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ የቆለላ አካባቢ የሙቀትና የአየሩ የርጥበት መጠን ይህንን ቴክኖሎጂ ውጤታማ ለማድረግ አመቺ መሆኑን ስራውን የሚሰሩት የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች አረጋግጠዋል፡፡

2. ሃገር በቀል እውቀቶችን ማሻሻያ በማከል ለገበያ ማቅረብ

በምዕራብ ጎጃም አካባቢ ታዋቂ፣ ተወዳጅ፣ ጥንታዊና ያለምንም ማቀዝቀዣ ለዓመታት መቆየት የሚችለውን የ"መጣጣ አይብ" አዘገጃጀት እውቀት በዘመናዊ የላቦራቶሪ ምርመራ በመታገዝ፣ አስፈላጊ የአዘገጃጀትና የአስተሻሸግ ቴክኖሎጂ በማከል እንዲሁም የምርት መግለጫ በመለጠፍ ለገበያ ለማቅረብ የተቋቀቋመው ቡድን ከመጣጣ ዓይብ በተጨማሪ የፈርመንቴሽን ሂደቱን ጨርሶ በአልኮልና በአንቲኦክሲዳንት ይዘቱ ከፍተኛነት የተነሳ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችለውን (ready to consume) ወይም ጊዜ በማይወስድ የአዘገጃጀት ሂደት ለመጠጥነት መዋል የሚችለውን "ድፍድፍ ጠላ" ወደ ገበያ ለማቅረብ በሚያመች መልኩ የአዘገጃጀት ሂደትና የአስተሻሸግ ቴክኖሎጂ እንዲሁም የምርት መግለጫ በማከል ለገበያ የሚቀርብበትን ሁኔታ በማጥናት ላይ ይገኛል፡፡

3. የስርዓተ ምግብ ሞዴል ክበብ ማቋቋም

መቀጨጭ፣ መከሳትና ለዕድሜያቸው ተገቢ ከሆነው ክብደት ያነሱ ህጻናት በከፍተኛ ቁጥር ከሚገኝባቸው ሃገሮች ኢትዮጵያ አንዷ ነች፡፡ በተለይ ደግሞ የቀጨጩ ህጻናት ቁጥር እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ በእነዚህ ህጻናት ላይ ሁኔታው በትምህርት አቀባበል፣ በተክለሰውነት ግንባታ እና ባህሪ ላይ የሚያደርሰው ከፍተኛ ጉዳት እነሱን ብቻ ሳይሆን የሃገርንም እድገት የሚጎዳ በመሆኑ ጉዳዩ ጊዜ የሚሰጠው አለመሆኑ ታውቋል፡፡ ችግሩን አስከፊ የሚያደርገው ሁኔታ ደግሞ የሰው ልጅ ከእርግዝና እስከ ሁለት ዓመት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ ተገቢውን አመጋገብ ካላገኘ በቀጣይ ህይወቱ ማስተካከል የማይችል መሆኑ ነው፡፡

ምንም እንኳን የቆለላ አካባቢ በምግብ ራሱን የቻለ ቢሆንም የሃብት መኖርና በምግብ ምርት ራስን መቻል ይህ ችግር እንዳይከሰት ዋስትና እንደማይሆን ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ችግሮቹ ከግንዛቤ ማነስ የተነሱ በመሆኑ ለማህበረሰቡ ስልጠና መስጠት አስፈልጓል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ዩኒቨርሲቲው በቆለላ ትምህርት ቤት ውስጥ የ"ስርዓተ ምግብ ክበብ" በማቋቋም የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስራ ጀምሯል፡፡

የእውቀትና ቴክኖሎጂ ስራዎች ያለቀላቸው ቴክኖሎጂዎችን ማሸጋገር ላይ ብቻ ያተኮረ እንዳለመሆኑ በሃገራችን በተለያዩ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችና ኢንተርፕራይዞች አብዛኞቹ ስራቸውን በእውቀት ላይ ተመስርተው ሳይሆን በተለምዶ የሚሰሩ በመሆኑ ደንበኞቻቸውን በማይቀያየር ሁኔታ ካለማርካታቸውና ጥራት መጠበቅ ካለመቻላቸው የተነሳ ከተሰማሩበት ዘርፍ ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም የማያገኙ በመሆኑ ባለሙያዎች ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ እየተሰጡ ካሉ እውቀት ላይ መሰረት ያደረጉ ስልጠናዎች የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

1.Yarn Pretreatment and Dyeing ለ15 የእናቶች ለእናቶች ኢንተርፕራይዝ አባላት

2. Designing, Pattern making, Cutting and Sewing of Garment ለ100 በዘርፉ የተሰማሩ የህግ ታራሚዎች

3. Cotton Yarn Dyeing training ለአውራምባ ማህበረሰብ

4. Weaving Efficiency Training ለአዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ

5. ከTechnoServe Ethiopia ጋር በመተባበር በMycotoxin Prevention and Control, Food Safety Management, Milling Technology & Baking Science በሚሉ ርዕሶች ላይ በአዲስ አበባ፣ ባህር ዳር እና አዋሳ በድምሩ ለ270 ስንዴ አቀነባባሪ ዱቄት ፋብሪካዎች፣ ዳቦ ቤቶችና ሌሎች መንግስታዊ ባለድርሻ አካላት ጭምር በተግባር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥተቷል፡፡

6. ከዩኒዶ ጋር በመተባበር በባህር ዳር፣ ወረታ እና ሐሙሲት ተበታትነው የሚገኙ የአነስተኛ ዘይት ጨማቂዎች የአመራረት ሂደት ማሻሻልና አስተሻሸግን አስመልክቶ ስልጠና መስጠት፤ እንዲሁም የጋራ ማንጠሪያ እንዲያቋቁሙ የአዋጭነት ጥናት ማጥናትና የአርኪቴክቸራል ስራ መገምገም ስራ እጅግ ውጤታማ እንደነበር ከዘይት ጨማቂዎቹ እርካታና በገበያው ላይ ካመጡት ለውጥ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## የባህር ዳር ሳይንስ ኢንኩቤሽን ማዕከል

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሚገኝበት ባህር ዳር ከተማና አካባቢው ውስጥ ባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በትምህርት ላይ የሚገኙ የልዩ ታለንንትና የፈጠራ ተሰጥኦ ባለቤት የሆኑ ታዳጊ ወጣቶችን በመመልመል ያላቸውን ታለንትና የፈጠራ ችሎታ ኮትኩቶ የሃገራችንን ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ምርምር የሚፈቱ የነገ ሳይንቲስቶችን ለመፍጠር ያስችላል ብሎ በማመን የሳይንስ ማዕከሉን በድልችቦ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በማቋቋም ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ስራ በአሜሪካዊ በጎ አድራጊ ሚስተር ማርክ ጌልፍላንድ ከፍተኛ እገዛ እየተደረገለት የሚገኝ ሲሆን የግንባታ ሂደቱ ተጠናቆ የቤተሙከራ ቁሳቁሶች ግዢ ሂደት ላይ ነው፡፡ ይህ ማዕከል ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ስራ እስኪጀምር ድረስ ዩኒቨርሲቲው የታለንት ኢንኩቤሽን ስራዎችን በተለያዩ ካምፓሶቹ በሚገኙ ቤተሙከራዎቹ ውስጥ በክረምት ወቅት በተበታተነ መልኩም ቢሆን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን እስካሁን ያገኘውን ልምድና የአዲሱን ማዕከል የስራ አመቺነት በመጠቀም ትርጉም ያለው ስራ እንደሚሰራበት ከፍተኛ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡




Knowledge is Experience [*practical application*],

Everything else is just Information

*Albert Einstein (1879-1955)*